# ኢትዮጵያና ሩዋንዳ በፐብሊክ ሰርቪስ አስተዳደር ስርዓት ግንባታ ላይ ተባብረው ለመስራት ተስማሙ፡፡

ኢትዮጵያና ሩዋንዳ ዘመናዊና ተገልጋይ ተኮር የፐብሊክ ሰርቪስ አስተዳደር ስርዓት በመገንባት ረገድ የልምድ ልውውጥ በማድረግ ተባብሮ ለመስራት ተስማምተዋል፡፡

ስምምነቱ የተካሄደው በኢፌዲሪ የሰው ሃብት ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አቶ አዳሙ አያና እና በሩዋንዳው የፐብሊክ ሰርቪስና የሰራተኛ ጉዳይ ሚኒስትር ጁዲት ኡዋዜ መካከል ነው።

የእድገትን ፍጥነት የሚመጥን አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ፐብሊክ ሰርቪስ መገንባት ካልተቻለ ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ እንደማይቻል ሁለቱ ወገኖች ባካሄዱት ውይይት ተገልጿል፡፡ ኢትዮጵያና ሩዋንዳ በፈጣን ሁኔታ በማደግ ላይ ከሚገኙ ሀገሮች መካከል የሚመደቡ እንደመሆኑ፣ ፐብሊክ ሰርቪሱን ብቁና ዘመናዊ በማድግ ረገድ ያላቸውን ልምድ በመለዋወጥ ለበለጠ ውጤታማነት በጋራ ለመስራት ተስማምተዋል፡፡

በልምድ ልውውጡ ትኩረት የሚደረግባቸውን መስኮች በመለየት፣ የድርጊት መርሃ ግብር የሚያዘጋጅ ቡድን በማቋቋም የኤክስፐርቶች የምክክርና የጉብኝት ልውውጥ ለማካሄድ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

ክቡር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ አዳሙ አያና ለ6ኛ ጊዜ በኪጋሊ ሩዋንዳ በመካሄድ ላይ ባለው የአፍሪካ ሲቪል ሰርቪስ ኮንፈረንስ ላይ ተገኝተዋል፡፡

*የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር*

*ቃልአቀባይ ጽ/ቤት*

*ሰኔ 16 ቀን 2009 ዓ.ም*

P.O.BOX 393 TEL: 011 5 517345 FAX: 011 5 514300 E-mail: mfa.press@ethionet.et Website: www.mfa.gov.et

P.O.BOX 393 TEL: 011 5 517345 FAX: 011 5 514300 E-mail: mfa.press@ethionet.et Website: www.mfa.gov.et